# ምጽአተ ማእበል

እባክህ አምላኬ ዝናቡን አውርደው
ተሰነጣጠቀ ደረቀብኝ ማሳው ፥
ይለምናል ጌታን ምስኪኑ ገበሬው።
ለከብቶቼ ግጦሽ ለልጆቼ ቆሎ።
ለግብር መክፈያ ማሽላ በቆሎ።
ፍጠን ድረስልኝ ዝናቡ ና ቶሎ ፥
ኤጭ ይሄ ዝናብ ተመልሶ መጣ።
አርፌ ልቀመጥ ደጅም አያስወጣ።
ጭቃ ብቻ ሆነ አያስኬድ መኪና።
ይህ አሮጌ ሰፈር ያልረባ ጎዳና።
ይላል ባለቪላው በረዳው ላይ ሆኖ
አፍንጫውን ሳይቀር በጋቢ ጀቡኖ
የዘንድሮው ዝናብ መነቸከ ባሰ።
ጣራው አረግርጎ ግድግዳው ፈረሰ፥
እባክህ ዝናቡ ተው ውረድ በቅጡ።
አትጨክን በድሃ አትሁንብን ቁጡ።
ትላለች በብሶት ጠላ ሻጭዋ ደሃ።
ድስት እየደቀነች ለፍሳሹ ውሃ፥
ዝናብም ልመና ይሰማል በቶሎ።
ይመጣል በርዶ ነፋስን ቀላቅሎ።
ነጎድጓድም ሳይቀርመብረቅ አስከትሎ።
በደረቁ ምድር አጉረምርሞ አለፈ።
ባረባው ጎዳና ሸክሙን አሳረፈ።
ግድግዳ አፈረሰ ጣራውን ነቀለ።
ለፈለገው ትቶ ላልፈለገው ጣለ።

ሠፍራ መለየትስ በቀልቡ የታለ፤

ይህንን የሰማ ያየ ያስተዋለ፤

ጬኸት አስተጋባ እሮሮው ቀጠለ፤

አይ ዝናብ አይ ዝናብ ያንተ ሠራ እያለ _ _ _

ደራሲም ተነሳ ብእሩን አሾለ፤

መከተቡን ያዘ ወረቀት ቆለለ፤
ርእሱን ሲሰይም ማእበል ነው አለ።

ከጌቱ ሀይሉ